## ፓኖራማ ቁጥር 79

–

## የትዝብት አድማስ

**ጥቅምት ቀን** 4 2002 **ዓም**

## በቁመናው ተበልቶ የሚያልቅ ሰብል

## በሕይወቷ እየተሸጠች የምትከስም ሀገር

*አዝመራየ ሲደርስልኝ ስብሉን ሽጨ ዕዳየን እከፍላለሁ በሚል ዕምነት ከአቅሙ በላይ የተበደረ አንድ ድሃ ገበሬ ፥ በአውድማው ወራት የሚከተለውን አዜመ ይባላል ፡፡*

> **" አወይ አንች ክምር አለሁን መስሎሻል፥**
> **ገና በቁመናሽ በብድር አልቀሻል፡፡ "**

*የዚህን ደሃ ገበሬ ስጋትና ጭንቀት፥ ዛሬ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እያነገራጎው ይገኛል፡፡ በዕለት ችግሩ ምክንያት ከአቅሙ በላይ የተበደረው ደሃ ገበሬ ፥ አዝመራውን በቁመናው በመሸጡ፥ቤተሰቡንና እራሱን ለማያባራ ችግር መጣሉን የተረዳው እጅግ ዘግይቶ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን ያጋጠመውን ችግር የተረዳው በጣም ዘግይቶ ነበር ለማለት ባይቻልም፥ ሀገሩን በቁመናዋ የሚሸጥ ኢትዮጵያዊ ቡድንና ትውልድ የመጣል ብሎ ያስብ እንደነበር ግን መገመት አይቻልም ፡፡ በጣም ጥቂቶች ኢትዮጵያውያን የወያኔን እውነተኛ ዓላማና ተግባር አስቀድመው አውቀው ለሕዝብ እንዳስጠነቀቁ ግን የሚካድ አይሆንም ፡፡ ያም ቢሆንም ቅሉ፥ እኛ አስቀድመን ተናግረን ስለነበር አሁን ወያኔ የሚሰራው ድርጊት ሊያስደንቀን አይችልም ብለው፥የኢትዮጵያን ሕዝብ ጭንቀት አይጋሩም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሀገር መጥፋት ተደራርቦ ሲመጣ ፥ ነቅቶ ያስጠነቀቀውም ሆነ ሰምቶ ያልተንቀሳቀሰው ሁሉ በጋራ ሀገሩን የማዳን እኩል ኃላፊነት ስለሚኖረው ነው ፡፡በተለየ ደግሞ ኢትዮጵያ፥ ሀገራዊ ጨገሬታዋ በሁሉም አቅጣጫዎች እየተቆራረሰ በሚሄድበት ጊዜ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ የሚያምነው ዜጋ ሁሉ ፥እኔን አይመለከተኝም ሊል ስለማይችል ነው፡፡ ወያኔዎቹ ዛሬ በኢትዮጵያ መልከዓ ምድር፥ ያሻቸውን ለማድረግ የሚያስችላው ሁኔታ ስለተመቻቸላቸው፥ ሀገሪቱን ቆርሶ ለመሸጥ ብቻ ሳይሆን፥ ሕዝቡን ከሀገሪቱ ጋር አብረው እንዳይሸልጉት የሚከለክላቸው ኃይል ስለሌለም ጭምር ነው ፡፡ በየትኛው የታሪክ ሂደትም ይሁን፥የፖለቲካ ርዕዮትና የመንግሥት ሥርዓት፥ የገዛ ሀገሩን ለባዕድ አሳልፎ የሚሸጥ በሥልጣን ያለ የተቀመጠ ቡድን ታይቶም ተሰምቶም ስለማይታው ነው፡፡ይህ ሀቅ ግን በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ለሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተጨባጭ ግልፅ ሆኖለታል ፡፡ የኢትዮጵያ መልከዓ ምድር ጃርት የበላው ዱባ እየመሰለ በመሄድ ላይ ይገኛል ፡፡አንድ ሰብል ገና በአዝመራው እያለ በቁመናው በብደር እንደሚሸለገው ሁሉ ፥ ኢትዮጵያም በቆመናዋ በየአቅጣጨው እየተሸራረፈች ትገኛለች፡፡ይህንን የሀገር መሸራረፍ ጉዳይ፥ደግመን ደጋግመን ለማውሳት የፈለግነው ፥ የሁኔታውን ክብደትና የሄደቱን ፍጥነት ሁሉም እንደኛ በአንክሮ ተመልክቶ ሀገሩን ከሽያጭ ለማዳን ቆርጦ እንዲነሳ በድጋሜ ለማሳሰብ ነው፡፡*

*አሁን በኢትዮጵያ መሬት የመሸጡን ጉዳይ አስመልክቶ በቅርቡ የወጣ አንድ ጥናት እንደሚያስረዳው ከሆነ ፥ በዚህ ወር ወያኔ ለሱዳን ለማስረከብ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ መሬት ስፋት፥* 64ሽ100 *ስኩዌር ኪሎ ሜትር ይሆናል ተብሏል ፡፡ ይህም ማለት ጅቡቲ ካላት የመሬት ስፋት በበዙ እጅ ይበልጣል ማለት ነው ፡፡ ይህን የኢትዮጵያ ለም መሬት*

ለባዕድ አሳልፎ መስጠት ማለት ሌላውን እንኳን አናቆየውና የረሃብተኛውን ሕዝባችንን ዳቦ መቀማት ብቻ ሳይሆን ፥ የእህል ጎተራውንም ጭምር ማዘረፍ ነው ። በታላላቅ ወንዞች የለመለመውን የወለጋንና የጎንደርን ለም መሬት ወደ ሱዳን ግዛት እንዲጠቃለል መፍቀድ፥ የኢትዮጵያ ዜጎች የሆኑ ግለሰቦች ይፈፅሙታል ብሎ የሚያመን ካለና ከነበረ ፥ በቅድሚያ የሥነአዕምሮ ዝግጅት አድርጎ የሚጠባበቅ ዜጋ ብቻ መሆን አለበት ። የወያኔ ሰዎች ይህንን የሚፈጽሙት፥ለኢትዮጵያና ለዜጎቿ ካላቸው ጥላቻ ብቻ ሳይሆን፥ቋጥረውት ከኖሩት የቂም በቀል መወጫም ጭምር መሆኑ ማንም ሊጠራጠር አይችልም። ይህንን ሀቅ የተገነዘበ ዜጋ ሁሉ በመነሳት ሀገሩን ለማዳን ካልቻለና እንዲያው በደፈናው አንዱ በሌላው ላይ ጣቱን እየተጠቋቆመ ከቀጠለ ፥ ነገ ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራ ሀገር ትኖረኛለች ብሎ ተስፋ ሊያደርግ የሚቻለው አይሆንም ። የጥንት አባቶችና እናቶች ያቆዩዋት ኢትዮጵያን ማንም አይደፍራትም ብሎ ገላውን ሰድዶ መቀመጥ ማለት፥ የዓለምን ሀገሮች መወለድና መሞት ታሪክና ሂደት አለመገንዘብ ይሆናል።የሀገሩን ኅልወናም ሆነ ነፃነት አስመልክቶ፥የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ከጥንት ጀምሮ የሚተማመነው በራሱ ብቻ እንደነበር፥ እርሱ እራሱ የሚያውቀው ሀቅ ነው ። የቅርብ ዘመን ተትዝታው እንደሚጠቁመው፥ በቀውጢ ቀን መሪዎቹ ጥለውት ሲሄዱ እርሱ ራሱ ባለቤቱ ተዋግቶናመስዋዕት ከፍሎ ሀገሩን ከጥፋት የሚያድናት መሆኑን በተጨባጭ አስመስክሯል ።ዛሬም የተለየ ሁኔታ ሊከሰት የሚችልበት ምክንያት አይኖርም ።

በአሁኑ ስዓት ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳየው፥ አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ድርጅቶች ትኩረት ያነጣጠረው፥ በዚህ ዓመት መጨረሻ አካባቢ በሚደረገው የወያኔ ምርጫ ላይ መሆኑ ይኸው እየታየ ነው ። ለብዙዎች የቅድሚያ አጀንዳ የሆነው በዚህ የወያኔ ምርጫ ዙሪያ ስንት መቀመጫና ምን ዓይነት የሥልጣን ፍርፋሪ ሊሰጠን ይችላል የሚል ሆኗል ። በመሆኑም የሀገር መሬት መሸጥም ሆነ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕልውና ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጡት ሆኖ አላገኙትም ። ሌላው ቀርቶ " መጀመሪያ የመቀመጫየን " ያለችውን የዱር እንስሳ የቅድሚያ አጀንዳ ተገንዝበው እንኳ፥ ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ኅልውና ይቀድም ለማለት አልተቸገሩም ። የትግልን አጀንዳ ቅደም ተከተል በሚገባ ያልተረዳ የፖለቲካ ድርጅት፥ መልኅቁን እንዳጣ መርከብ ከመዋለል የተለየ ዕድል ሊገጥመው አይችልም ። በተለይም ደግሞ ፥የተቃዋሚ ድርጅት ነኝ ብሎ ለሕዝብ ያሳወቀ የፖለቲካ ቡድን ፥ ሕዝባዊና ሀገራዊ መሆኑን የሚገልጽበት የቅድሚያ አጀንዳ ፥ ኖሮት የሕዝብ ወገተኝነቱን በእንቅስቃሴ ካልገለፀ ፥ የአምባገነኖች ተቀፅላና ግብረ-አበር ከመሆን አይተርፍም ። ወያኔም የሚፈልገው ይህን ዓይነቱን ነው ።በተለይማ፥በወያኔ አጀናዳና ድርጊት ዙሪያ እየተሽከረከሩ ፥የአጀንዳው ምላሽ ሰጭና የድርጊቱ ዳንኪራ ረጋጮች ከሆኑለት ይደሰትባቸዋል ። የዕድሜ ቀጣይነታቸውንም ሚና አበክሮ ይወድላቸዋል ። ሕጋዊ ተቃዋሚዎችም የሚል ቁርባነ-ወያኔ ሰጥቶ ያፍነሸንሻቸዋል ። ከዚያ በኋላማ ፥ የኢትዮጵያ ኅልውና ፥ የዜጎቿ ነፃነትና አንድነት፥ ሀገራዊ ልዕልና የሚባል ጉዳይ ደብዛው እየጠፋ ይሄዳል ። ዛሬ በአብዛኛው በሀገራችን የፖለቲካ መድረክ የሚሰማው መፈክር --፤

" የበላ በለጠኝ የሮጠ ቀደም " ሆኗል። ከታሪክ አለመገንዘብ ሆኖ ነው እንጅ፥ብቻውን የበላ ብቻውን እንደሚሞት፥ ሀገር ጥሎ የሮጠም ብቻውን ተዋርዶ እንደሚጠፋ ከወያኔ በፊት የነበሩት የሁለት ሥርዓት አራማጆች የቅርብ ትዝታዎች ሆነዋል ። መጀመሪያ የሀገሪቱን ቅስ በቅስ እየተሸጠች መጥፋት ከልብ የተገነዘበ ሁሉ ሁኔታውን ለመለወጥ መነሳት አለበት። ሁኔታውን ለመወጥ የሚያስችል የቅድሚያ አጀንዳ ሊኖር ግዴታ ይሆናል ። ኢትዮጵያን ለማዳን ከተፈለገ፥ ከሁሉ በፊት የጥፋቷ ምክንያትና ተጠያቂ የሆነውን ቡድን ማስወገድ ነው ። ይህን ስኬታማ ለማድረግ ካስፈለገ የትግሉ ሁሉ የመጀመሪያው አጀንዳ አድርጎ መንቀሳቀስና በዚሁ ለይ መረባረብ ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ አይሆንም። የኢትዮጵያን መሬት ለባዕድ ለመሸጥ የቅድሚያ አጀንዳው አድርጎ የሚነቀሳቀሰውን ከሀዲ ቡድን በራሱ ፓርላማ ውስጥ እየተቃወሙ ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን ይቻላል ብለው የሚያስቡ ካሉ፥ ራሳቸውን ሊመረምሩ ይገባል ። የቅድሚያ አጀንዳቸውን በወያኔ ፓርላማ ምርጫ መወዳደር ላይ ያተኮሩ ክፍሎች፥ በኋላ በፈርስ ላይ ማኋኀር እንዳይሆንባቸው ሊያስቡበት ይገባቸዋል።

“ ገላጋይ አጥቼ ልጄን ደብድቤ ገደልኩት ። ” ብሎ እንደተፀፀተው አባት ፥“ የቅድሚያ አጀንዳችንን ኢትዮጵያን ማዳን ሳናደረግ በመቅረታችን ፥ ኢትዮጵያ ቀስ በቀስ ተሸራርፋ ቀረች። ” እያሉ የአሶ እንባ ቢያለቅሱት ፥ የሀገራችንን ሀዘንተኛ ልብ አያፅናናውም።

የወያኔ ቡድን ሀገሪቱን ቀስ በቀስ ለማጥፋት ምርኩዝና ማጠየቂያ ያደረጋቸው ሁለት ዓይነተኛ መሳሪያዎችን እንደ ድልዳል ለመጠቀም እየሞከረ ነው ። የኋላ ኋላ ሁለቱም ጠፍተው እርሱንም እንደሚያጠፉት ግን አልተገነዘበውም ። የመጀመሪያ ድልዳሉ ፥ የወያኔንን ዝባዝንኪ የፖለቲካ ፕሮግራም እንደ ሀገሪቱ ሕገመንግሥት ቆጥሮ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈፀመው ብሔራዊ ወንጀል የህግ ድጋፍ እንዳለው ለማስመሰል የሚያደርገው ከንቱ፥ የከንቱ ከንቱ መፍጨርጨር ነው ። የአምባገነኑ የደርግ ሥርዓት የጻፈው ጨቋኝ ሕገመንግሥት፥ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሲፈረጥጥ ተቀዳድዶ እንደወደቀው ሁሉ ፥ የወያኔዎቹም ሕገመንግሥት ነገ ከእነርሱ ጋር የዶግ አመድ ሆኖ እንደሚቀር ኢትዮጵያዊው ሁሉ አይጠራጠርም ። ሁለተኛው የወያኔ ድልዳልና የወንጀሉ አባሪ ተባባሪ አድርጎ ለመጠቀምም የሚከጅለው በ “ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ” ሽፋን ያደራጀው የወያኔ ታጣቂ ኃይል ነው ። ከመስመር መኮንኖች ጀምሮ እስከ ጀኔራል መኮንኖች ድረስ በራሱ አምሳልና አካል የቀረፀውና በራሱ ብሔር አባላት የሚታዘዘው ሠራዊትን እንደ አሻኝ አድርጌ እጠቀምበታለው ብሎ ያስባል ። ይህ ሠራዊት ግን ውሎ አድሮም ቢሆን አፈሙዙን ወደ ወያኔ መሪዎች እንደሚያዞር የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉጉት የሚጠብቀው ተስፋ ሆኗል ። ያ ተፈፀመ አልተፈፀመ ግን ፥ ይህ በአንድ ብሔር ቁጥጥር ስር ያለ ሠራዊት፥ ወያኔን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና ፍርድ ሊያድነው አይችልም። ከሳሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ተወዳዳሪ የሌለው የኢትዮጵያ ሠራዊት ደርግን ከመጥፋት እንዳላደነው ሁሉ፥ የወያኔንም ወንጀለኞች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣ ሊያድናቸው የሚችል ምድራዊ ኃይል አይኖርም ። ይህም ወደፊት የሚታይ ይሆናል ። እስከዚያው ድርስ ግን ትኩረትና ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ብሔራዊ አጀንዳ ፥ ከቀን ወደቀን ጎልውናዋ በመክሰም ላይ ያለችውን ኢትዮጵያን ማድን ነው ብለን እናምናለን። በዕርግጥም፥ ቁመናዋ እየከሰመ የምትጠፋውን ሀገር ከማዳን የበለጠ ሌላ ብሔራዊ ተግባር አይኖረንም !!!